# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 1-10/2021 የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ከኦክቶበር 11-20/2021 የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ መጽሄት

ኦክቶበር 2021
አዲስ አበባ

**ማውጫ** **ገፅ**

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 2
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት ........ 3
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 4
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 4
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 5

በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 5
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ........ 6

ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የሚኖረው የአየር ........ 7

ሁኔታ አዝማሚያ ........ 7

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 7

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ዝቅተኛዉ የአየር ግፊት የአረብ ባህር ላይ በተደጋጋሚ በመስተዋሉ ዕርጥበታማዉ የአየር ሁኔታ ወደ ሀገራችን እንዲገባ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም በምስራቅ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎችም የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት አብዛኛዉ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ምዕራብና ማካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የአፋር ደቡባዊ ክፍል፣ የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና የምስራቅ ኢትዮጵያ ሰሜን ሱማሌ፣ ሐረሪና ድሬዳዋ በብዙ በቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በአማራ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ አንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በመተሓራ 36.0፣ በጊዳ አያና 36.0፣ በቦሬ 34.7፣ በኢጃጂ 70.6፣ በካቺስ 38.4፣ በሻምቡ 30.2፣ በጊኒር 42.0፣ በጃራ 37.8፣ በበደሌ 57.8፣ በቡሌ ሆራ 38.4፣ በቴፒ 36.8፣ በቡኢ 47.0፣ በደባርቅ 39.4 እና በደብረወርቅ 39.7 በሚሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከጥቂት የሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ(03) በስተቀር በተቀሩት የአማራ ክልል ዞኖች፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ዞን 02፣ 03፣ 04ና 05፣ ከጥቂት የቦረናና ሰሜን ሸዋ(04) በስተቀር በተቀሩት የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ላይ፣ በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና ሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል በሲቲና ፋፈን እንዲሁም በደገሃቡር ዞኖች ላይ ከ25-177 ሚሜ. የሚደርስ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከ5-25 ሚሜ. ከ4 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአንዳንድ የቦረና፣ ጉጂና ባሌ ቆላማ ቦታዎች በስተቀር በተቀሩት የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፣ ከጥቂት የሰሜን ወሎ ዞን በስተቀር በተቀሩት የአማራ ክልል ዞኖች፣ በአፋር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሁሉም ዞኖች እንዲሁም በሲቲ፣ በፋፈን፣ በደገሃቡርና ፊቅ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር  1 እስከ 10 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት




ካርታ 3   ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10 /2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የበጋው ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በጥቂት የሰሜንና የሰሜን ምሰራቅ ጥቂት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረ ቢሆንም፤ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፋ እርጥበት እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተጨማሪም በምስራቅ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎችም የተለያየ መጠን ያለው እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ በአጠቃላይ ባሳለፍናቸው የኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የተስተዋለው የአየር ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የግብርና እንቅስቃሴ ላይ የተለያየ ተጽዕኖ እንደነበረው መገንዘብ ይቻላል። በተለይም ደረቅ ሆነው በሰነበቱት ጥቂት የሰሜንና የሰሜን ምሰራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለደረሱና በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ሰብሎች ደረቅና ነፋሻማ የነበረው የአየር ሁኔታ አዎንታዊ ሚና የነበረው ቢሆንም፤ በሌላ መልኩ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ፣ የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎቸ ላይ የነበረው እርጥበታማ ሁኔታ ቀደም ብለው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱ፣ አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፤ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች ገንቢ ሚና የነበረው ሲሆን፤ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተወሰነ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚካሄድባቸው በደቡብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ዘር ለመዝራትና እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደርች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ኦክቶብር 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ እርጥበት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በከፊል የምዕራብ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛዉ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የላይኛዉና የመካከለኛዉ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛዉ ገናሌዳዋ፣ ዋቢሸበሌ እንዲሁም የላይኛዉና የመካከለኛው አባይ ተፋሰሶች ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ አግኝተዋል። በተጨማሪም በአብዛኛው የላይኛዉ አባይ፣ በጥቂት የታችኛዉ ኦሞጊቤ እና ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የታችኛዉ ገናሌዳዋ እና መካከለኛዉ አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው። የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሎ ነበር (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የአየር ሁኔታ ገፅታዎች ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የምዕራብና የደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ኪስ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ቀሪዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች በአመዛኙ ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ስር ሊቆዩ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ አርሲና ባሌ፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ ምዕራብ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ምዕራብ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የጌዲዮ፣ የጉራጌ፣ የጋሞና የጎፋ ዞኖች፤ እንዲሁም የሲዳማ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል ፋፈን፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና የሸበል ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ከሚፈጠሩ ደመናዎች በሰሜንና ደቡብ ወሎ፤ በሰሜን ምዕራብ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ትግራይ፤ ከአፋር ዞን 3፣4 እና 5፤ ጥቂት የሰሜን ቦረናና የጉጂ ዞኖች፣ የምዕራብና የምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፤ ሐረሪ፤ ጋምቤላ፤ የደቡብ ኦሞና የሰገን ህዝቦች እንዲሁም በአዲስ አባባ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ ዝናብ ይኖራል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦክቶበር የሁለተኛዉ አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በአብዛኛው ለግብርናው ዘርፍ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ ዕድገት የሚያስፈልጋቸውን የእርጥበት ፍላጎት ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የእርጥበት ሁኔታው ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ወደ ደቡብ የሚያደርገው መስፋፋት ለደጋማ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአካባቢው ለሚኖሩት

አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የታመናል። በተጨማሪም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማችት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በአንፃሩ በተቀሩት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ወቅት ደረቅ ፀሓያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ በተለይም በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ሰብሎች አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፤ በሌላ መልኩ በተለለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላላጠናቀቁ እንዲሁም ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸው ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች አሉታዊ ጎን እንደሚኖረው ይጠበቃል።

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ በአብዛኛው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመለክታል። ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ የደቡባዊና የምዕራባዊ አጋማሽ አባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤና ስምጥሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች እርጥበታማ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ዉስጥ የመካከለኛውና የታችኛው አዋሽ፣ ምስራቃዊ አባይ፣ የላይኛው ተከዜ፣ የታችኛው ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ፣ የታችኛው ባሮአኮቦ እና የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፍል ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡